# በስቶክሆልም የኢትዮጵያ ኤምባሲ የመንግሥት የጋራ መኖሪያ ቤቶች ምዝገባ

በአገራችን የመንግሥት ሠራተኛውንና ዝቅተኛ ገቢ ያለውን የከተማ ነዋሪ የቤት ባለቤት ለማድረግ መንግሥት በክልሎች እና በአዲስ አበባ እና በድሬዳዋ ከተሞች ከ2000 ዓ.ም ጀምሮ በ20/80 ኮንዶሚኒየም ቤቶች ኘሮግራም የመኖሪያ ቤቶች ገንብቶ ለነዋሪዎች ሲያስረክብ ቆይቷል፡፡

የከተሞች የመኖሪያ ቤት ፍላጐት በየጊዜው እየጨመረ በመምጣቱ ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ ፕሮግራሙን በማስፋት በ10/90፣ በ20/80 እና 40/60 ኘሮጀክቶች እንዲሁም በማህበራት ተደራጅተው ለሚቀርቡ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች የመኖሪያ ቤት ገንብቶ ለማቅረብ ምዝገባ ተካሂዶ በአሁኑ ጊዜ በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ የመኖሪያ ቤቶች ለነዋሪዎች ማስረከብ የተቻለ ሲሆን ቀሪውን የመኖሪያ ቤት ግንባታ በማጠናቀቅ ለማስረከብ ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡

በተመሳሳይ መልኩ በውጭ አገር የሚኖር ኢትዮጵያዊና ትውልደ ኢትዮጵያዊ የዚህ ኘሮግራም አካል እንዲሆን ለማድረግ መንግሥት የተለያዩ የዝግጅት ሥራዎችን ሲሰራ ቆይቶ በአሁኑ ወቅት የጋራ መኖሪያ ቤት ኘሮግራም ተጠቃሚ መሆን የሚፈልጉ ኢትዮጵያዊያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን የእድሉ ተጠቃሚ እንዲሆኑ በኢትዮጵያ ሚሲዮኖች በኩል ምዝገባ እንዲከናወን መመሪያ ተላልፏል፡፡

በዚሁ መሠረት ኤምባሲያችን በጋራ የመኖሪያ ቤት ኘሮግራሙ በግልም ይሁን በማህበር ተደራጅተው የቤት ባለቤት መሆን ለሚፈልጉ በስዊድን፣ በኖርዌይ፣ በዴንማርክ፣ በፊንላንድና አይስላንድ ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን ምዝገባ ለማካሄድ ዝግጅቱን ያጠናቀቀ ሲሆን ከምዝገባው በፊት በምዝገባ ሂደቱ ላይ የተሟላ ግንዛቤ እንዲፈጠር የኤምባሲውን ድረ ገጽና ማኅበራዊ ሚዲያዎችን በመጠቀም ዝርዝርና ግልጽ የሆነ መረጃ (የምዝገባ መስፈርቶች፣ የቤቶች አይነትና ስፋት፣ የግንባታ ዋጋ ግምት፣ የባንክ አካውንት አከፋፈት፣ የክልሎች ሞዴል የጋራ መኖሪያ ቤት ማህበራት መተዳደሪያ ደንብ፣ ዝቅተኛው የአንድ ማህበር አባላት ብዛት፣ የዲዛይንና ግንባታ ሁኔታን) ከዚህ እንደሚከተለው እያቀረብን፣ ከዚህ በተጨማሪ ምዝገባውን ከመጀመራችን በፊት ትክክለኛና የተሟላ ግንዛቤ እንዲኖር በስቶክሆልም፣ ኦስሎ፣ ኮፐንሃገንና ሄልሲንኪ ከተሞች በመኖሪያ ቤት ኘሮግራምና የምዝገባ ሂደት ላይ በቅርቡ የውይይት መድረክ በማዘጋጀት በየከተማው ከሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና ትውልድ ኢትዮጵያዊያን ጋር ውይይት በማካሄድ በአጠቃላይ ፕሮግራሙ ዙሪያ የተሟላ ግንዛቤ በመፍጠር ወደ ምዝገባ እንደምንገባ ከወዲሁ እናሳውቃለን፡፡

NB:

- በአሁኑ ጊዜ የመመዝገቢያ መመሪያቸው የደረሱንና ምዝገባም የምናካሂደው የትግራይ፣ የአማራ፣ የኦሮሚያ፣ የደቡብ፣ የሱማሌ፣ የሐረሪ፣ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል እና የጋምቤላ ክልሎች እንዲሁም የድሬደዋ ከተማ አስተዳደር ሲሆኑ የአፋር ክልል እና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር የምዝገባ ማስፈጸሚያ መመሪያዎች እንደደረሱን ምዝገባውን የምናከናውን መሆኑን እንገልጻለን፡፡
- በአዲስ አበባ ከተማ እና በአፋር ክልል የጋራ መኖሪያ ቤት ፕሮግራም መመዝገብ የሚፈልጉ የዲያስፖራው አባላት የክልሉና የከተማው የምዝገባ መመሪያ ተጠናቆ እስኪመጣ መጠበቅ የሚችሉ መሆኑን እያስታወቅን፣ በአጠቃለይ የጋራ መኖሪያ ቤት

ፕሮግራም፣ የምዝገባ ሂደትና የቤት ዓይነት ላይ የሚሰጠው መረጃ እና በውይይት መድረክ የሚቀርብ ገለጻ ተመሳሳይ በመሆኑ ከወዲሁ ግንዛቤ እንዲኖራችሁ እናሳስባለን፡፡

- ከዚህ ቀደም የተመዘገቡ ነባር የጋራ መኖሪያ ቤት ማህበራት የተመዘገቡበትን ማስረጃ፣ የማህበራት ማደራጃ ሰርተፍኬትና ገንዘብ በዝግ ሂሳብ በባንክ ያስቀመጡበትን ማስረጃ ሲያቀርቡ እንደ ነባር ማህበራት ተቆጥረው ቅድሚያ ተሰጥቷቸው የሚመዘገቡ ሲሆን ይህን ማስረጃ ማቅረብ የማይችሉ ነገር ግን በማህበር ተደራጅተው በጋራ መኖሪያ ቤት ግንባታ ለመሳተፍ ያመለከቱ ማህበራት በሙሉ እንደ አዲስ የጋራ መኖሪያ ቤት ማህበር የሚመዘገቡ ይሆናሉ::

- ከዚህ ቀደም በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የውጭ ምንዛሪ አካውንት የከፈቱ የዲያስፖራ አባላት በቤት ምዝገባ ወቅትም የሚያስፈልገውን ክፍያ ለመፈጸም ቀደም ሲል የከፈቱትን የውጭ ምንዛሪ አካውንት መጠቀም የሚችሉ ሲሆን እስከ አሁን የውጭ ምንዛሪ አካውንት ያልከፈቱ የቤት ምዝገባ ፈላጊዎች በመመሪያው ላይ በተቀመጠው መስፈርት መሰረት በምዝገባ ወቅት የሚያስፈልገውን የቤት ግንባታ የገንዘብ መጠን ክፍያ አስቀድሞ መፈጸም እንዲችሉ በኤምባሲው በኩል ከወዲሁ የውጭ ምንዛሪ አካውንት እንዲከፍቱ እናሳስባለን፡፡ የባንክ አካውንት ለመክፈት የተቀመጠውን መስፈርት የሚያሟሉ የዲያስፖራ አባላት በኤምባሲው ድረ ገጽ ላይ የተቀመጠውን የውጭ ምንዛሪ አካውንት ማመልከቻ በጥንቃቄ በመሙላትና በመፈረም ከሌሎች ተያያዥ ማስረጃዎች (የባንክ ሂሳብ ለመክፈት በመመሪያው የተቀመጠ መስፈርት) ጋር በፖስታ ቤት በኩል ለኤምባሲው ከላኩ የባንክ አካውንቱ በአስቸኳያ ተከፍቶ በአመልካቹ የስልክ ወይም የኢሜይል አድራሻ እንዲገለጽ ይደረጋል፡፡

# የመንግሥት የጋራ መኖሪያ ቤቶች ምዝገባ

## 1. ለምዝገባ ብቁ የሚያደርጉ መስፈርቶች

በግል ተመዝግበውም ሆነ በመኖሪያ ቤት ሕብረት ሥራ ተደራጅተው ቤት ለመገንባት ፍላጐት ያላቸው በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት ይኖርባቸዋል፡፡

### 1.1 ለኢትዮጵያውያን

- የፀና ፓስፖርት ቅጂ፣
- የሚኖርበት አገር የመኖሪያ ፈቃድ ወይም የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ አደረጃጀቶች ባሉባቸው አገሮች የኮሚኒቲ ማህበር አባልነት መታወቂያ ካርድ ወይም በሚሲዮኑ ተረጋግጦ የሚሰጥ ማስረጃ፣
- ያገባ ከሆነ/ች ማስረጃ ዋናውንና ቅጂውን፣
- ሁለት ፓስፖርት መጠን ፎቶግራፍ፣
- ለምዝገባው የተዘጋጁ ቅጾችን ሞልቶና ፈርሞ ማቅረብ፣
- ከዚህ በፊት በራሱም ሆነ በትዳር ጓደኛ ስም በመረጡት ክልል/ከተማ አስተዳደር ውስጥ የመኖሪያ ቤትም ሆነ የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ የሌለው ወይም ኖሮት ለሦስትኛ ወገን ያላስተላለፈ፣
- የቤቱን ግንባታ ወጪ 50% በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በኩል በውጭ ምንዛሪ /በዶላር፣ በዩሮ፣ በፓውንድ/ በግል የባንክ ሂሳብ በመከፈት የሚያስቀምጥና መሬት ተዘጋጅቶ ለማህበሩ ሲሰጥ ቀሪውን 50% ሙሉ በሙሉ በመክፈል የግንባታ ፈቃድ ለመውሰድ ዝግጁ የሚሆን፣
- የቤቱን ግንባታ ወጪ 50% በውጭ ምንዛሪ አገር ውስጥ በግል የባንክ ሂሳብ ገቢ ያደረገበትን ደረሰኝ ቅጂ የሚያቀርብ፣

### 1.2 ለትውልድ ኢትዮጵያውያን

- የፀና ፓስፖርት ቅጅ፣
- የፀና የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ ቅጅ፣
- ያገባ ከሆነ/ች ማስረጃ ዋናውንና ቅጂውን፣
- ለምዝገባው የተዘጋጁ ቅጾችን ሞልቶና ፈርሞ ማቅረብ፣
- ከዚህ በፊት በራሱም ሆነ በትዳር ጓደኛው ስም በመረጡበት ክልል/ከተማ አስተዳደር ውስጥ የመኖሪያ ቤትም ሆነ የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ የሌለው ወይም ኖሮት ለሦስተኛ ወገን ያላስተላለፈ፣
- የቤቱን ግንባታ ወጪ 50% በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በኩል በውጭ ምንዛሪ /በዶላር፣ በዩሮ፣ በፓውንድ/ የባንክ ሂሳብ በመከፈት የሚያስቀምጥና መሬት ተዘጋጅቶ ለማህበሩ ሲሰጥ ቀሪውን 50% ሙሉ በሙሉ በመክፈል የግንባታ ፈቃድ ለመውሰድ ዝግጁ የሚሆን፣
- የቤቱን ግንባታ ወጪ 50% በውጭ ምንዛሪ አገር ውስጥ በግል የባንክ ሂሳብ ገቢ ያደረገበትን ደረሰኝ ቅጂ የሚያቀርብ፣

### 1.3 ተመላሽ የዳያስፖራ አባላት

#### 1.3.1 ኢትዮጵያውያን ተመላሽ የዳያስፖራ አባላት

ኢትዮጵያዊ ተመላሽ የዳያስፖራ አባላት ከተመለሱ ከሁለት ዓመት በታች ከሆነ የሚከተሉትን ሲያሟሉ ብቻ በውጭ ምንዛሪ ክፍያ መመዝገብ ይችላሉ፡፡

- የፀና ፓስፖርት ዋናውንና ቅጂውን፣
- ውጭ አገር የኖረ ስለመሆኑ የሚያሳይ ማስረጃ፣
- አገር ውስጥ ከሁለት ዓመት በላይ ያለመኖሩ የሚያሳይ ማስረጃ ዋናውንና ቅጂውን ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በማቅረብ ማስረጃ ሲሰጠው፣
- ከዚህ በፊት በራሱም ሆነ በትዳር ጓደኛ ስም በመረጡት ክልል/ከተማ አስተዳደር ውስጥ የመኖሪያ ቤትም ሆነ የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ የሌለው ወይም ኖሮት ለሦስተኛ ወገን ያላስተላለፈ፣
- የቤቱን ግንባታ ወጪ 50% በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በኩል በውጭ ምንዛሪ /በዶላር፣ በዩሮ፣ በፓውንድ/ የባንክ ሂሳብ በመክፈት የሚያስቀምጥና መሬት ተዘጋጅቶ ለማህበሩ ሲሰጥ ቀሪውን 50% ሙሉ በሙሉ በመክፈል የግንባታ ፈቃድ ለመውሰድ ዝግጁ የሚሆን፣
- ከላይ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ በአገር ውስጥ በአለም አቀፍ/አህጉራዊ ድርጅቶች፣ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ባልሆኑ በግል ድርጅቶች ውስጥ ተቀጥሮ የሚሰራና ወርሃዊ ክፍያው በኢትዮጵያ ብር ከሆነና ግብር ከፋይ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በማቅረብ ሲሰጠው፣
- በጡረታ ተገልለው ወደ አገር ቤት ተመልሰው የሚኖሩ ጡረታቸው በባንክ በኩል ወይም በውጭ ምንዛሪ ገቢ ሆኖ በብር የሚከፈላቸው መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ሲያቀርቡ በኢትዮጵያ ብር ከፍለው መመዝገብ ይችላሉ፡፡

#### 1.3.2 ትውልድ ኢትዮጵያውያን ተመላሽ የዳያስፖራ አባላት

በአገር ውስጥ በተለያዩ የኢንቨስትመንት፣ የንግድ፣ በአለም አቀፍ/አህጉራዊ ድርጅት፣ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶችና በሌሎች የግል ሥራዎች ጭምር የተሰማሩና ሁለት ዓመትና ከዚያ በላይ እየኖሩ ያሉ ትውልድ ኢትዮጵያውያን የሆኑ ተመላሽ የዳያስፖራ አባላት የሚከተሉትን ሲያሟሉ ብቻ በኢትዮጵያ ብር ከፍለው መመዝገብ ይችላሉ፡፡

- የፀና ፓስፖርት ቅጅ፣
- የፀና የትውልድ ኢትዮጵያዊ መታወቂያ ካርድ ዋናውንና ቅጂ፣
- አገር ውስጥ ቢያንስ ሁለት ዓመትና ከዚያ በላይ መኖሩን የሚያሳይ ማስረጃ ዋናውንና ቅጂውን ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በማቅረብ መረጃ ሲሰጠው፣
- ከዚህ በፊት በራሱም ሆነ በትዳር ጓደኛው ስም በመረጡበት ክልል/ከተማ አስተዳደር ውስጥ የመኖሪያ ቤትም ሆነ የመኖሪያ ቤት መስሪያ የሌለው ወይም ኖሮት ለሦስተኛ ወገን ያላስተላለፈ፣
- በጡረታ ተገልለው ወደ አገር ቤት ተመልሰው የሚኖሩ ጡረታቸው በባንክ በኩል ወይም ምንዛሪ ገቢ ሆኖ በብር የሚፈለግባቸው መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ሲያቀርቡ በኢትዮጵያ ብር ከፍለው መመዝገብ ይችላሉ፡፡

- የቤቱን ግንባታ ወጪ 50% በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በኩል በውጭ ምንዛሪ /በዶላር፣ በዩሮ፣ በፓውንድ/ የባንክ ሂሳብ በመክፈት የሚያስቀምጥና መሬት ተዘጋጅቶ ለማህበሩ ሲሰጥ ቀሪውን 50% ሙሉ በሙሉ በመክፈል የግንባታ ፈቃድ ለመውሰድ ዝግጁ የሚሆን፣

**2. <u>የምዝገባ ቦታ</u>**

- በስቶክሆልም እና አካባቢው ከተሞች የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን የሚመዘገቡት ኤምባሲው ዘንድ በአካል በመገኘት ብቻ ነው፡፡
- በስዊድን ዮቶቦሪ ከተማና አካባቢው ከተሞች የሚገኙ የዳያስፖራ አባላት በዮቶቦሪ ከተማ ኤምባሲው በሚያመቻቸው ቦታ በአካል በመገኘት ይመዘገባሉ፡፡
- ከዚህ በተጨማሪ በስዊድን ከርቀት አንጻር ኤምባሲው ዘንድ በአካል ቀርበው መመዝገብ የማይችሉ በሰሜን ስዊድን ከተሞች የሚኖሩ የዳያስፖራ አባላት ኤምባሲው በሚያመቻቸው ማእከላዊ ቦታና በሚወስነው ጊዜ ውስጥ መመዝገብ ይችላሉ፡፡
- በኖርዌይ፣ በዴንማርክ፣ በፊንላንድ እና አይስላንድ የሚኖሩ የኢትዮጵያ ዲያስፖራ አባላት በየአገሩ ዋና ከተሞች ኤምባሲው በሚያመቻቻው ቦታ በአካል በመገኘት ይመዘገባሉ፡፡
- ተመላሽ የዳያስፖራ አባላት በመረጡት ክልል/ከተማ አስተዳደር በአካል በመገኘት መመዝገብ ይችላሉ፡፡

**2.1 በግል የመኖሪያ ቤት ተመዝጋቢዎች**

- በግል የሚመዘገቡ የዳያስፖራ አባላት የሚፈልጉትን ክልል/ከተማ አስተዳደር በመምረጥ የሚፈልጉትን የቤት አይነት ይመርጣሉ፣
- ቤቱን ለመገንባት ከሚያስፈልገው ወጪ ውስጥ የሚጠበቅባቸውን 50% ክፍያ በምዝገባ ወቅት ከሚኖሩበት አገር በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የውጭ ምንዛሪ የግል ሂሳብ በመክፈት ገንዘብ በውጭ ምንዛሪ ወደ አገር ቤት በመላክ ወደተከፈተው አካውንት ያስተላለፉበትን ደረሰኝ ቅጂ ተሞልቶ ከተፈረመው የመመዝገቢያ ቅጽ ጋር በማያያዝ ለሚሲዮኑ ያቀርባሉ፡፡
- በግል የተመዘገቡ የዳያስፖራ አባላት በመረጡት ክልል/ከተማ አስተዳደር የማህበራት አደረጃጀት መመሪያ መሠረት ዝቅተኛውን ቁጥር ሲያሟሉ ኤምባሲው በማህበር እንዲደራጁ በማድረግ መረጃውን ወደ ዋናው መስሪያ ቤት የዳያስፖራ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጀኔራል ይልካል፡፡
- የግል ተመዝጋቢዎችን በተመዘገቡበት ሚሲዮን /በሚኖሩበት አገር/ በመረጡት ክልል/ከተማ አስተዳደር የአደረጃጀት መመሪያ መሠረት በማህበር ዝቅተኛውን ቁጥር የማይሞሉ ከሆነ ከኤምባሲው መረጃቸው በሸኚ ደብዳቤ ለዳያስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጀኔራል ይላካል፡፡
- በግል የመጡ መረጃዎችን ወደ መረጡት ክልል/ከተማ አስተዳደር በዳያስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጀኔራል አማካኝነት ይላካል፡፡
- ክልሉ/ከተማ አስተዳደሩ በተመሳሳይ መልኩ ከሌላ ሚሲዮን ዝቅተኛውን የማህበር አባላት ቁጥር ሳይሞሉ ከተላኩት ጋር በማህበር እንዲደራጁ በማድረግ መረጃውን ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርና ለተወካዮቻቸው ያሳውቃል፡፡

**2.2 በመኖሪያ ቤት ሕብረት ሥራ ማህበር ተደራጅተው የሚመዘገቡ የዳያስፖራ አባላት**

- በመጀመሪያ መደራጀት የሚፈልጉበትን ክልል/ከተማ አስተዳደር ይመርጣሉ፣
- በመረጡት ክልል/ከተማ አስተዳደር የአደረጃጀት መመሪያ መሠረት የአባላቱን ቁጥር ይወስናሉ፣

- የመስራች ስብሰባ በመጥራት በመረጡት ክልል/ከተማ አስተዳደር የማህበራት መተዳደሪያ ደንብ መሠረት የማህበራቸውን መተዳደሪያ ደንብ አዘጋጅተው ያፀድቃሉ፣ ማህበሩን ይመሰርታሉ፣
- በምስረታ ስብሰባው የሥራ አመራር ም/ቤት፣ የሥራ አመራር ኮሚቴ፣ የቁጥጥር ኮሚቴ፣ የቴክኒክና የማህበራዊ ኮሚቴ እና እንደአስፈላጊነቱ ሌሎችንም ኮሚቴዎች ያቋቁማሉ፡፡ የአመራር አባላትም ምርጫ ያደርጋሉ፡፡
- ሁሉም የማህበሩ አባላት የመስራች ስብሰባ ቃለ-ጉባኤ፣ የመተዳደሪያ ደንብ እና የመስራች አባላት ዝርዝር ቅጽ ላይ ፊርማቸውን ያኖራሉ፣
- ማህበሩ በሕጋዊ መንገድ በመኖሪያ ቤት ሕብረት ስራ ማህበር መመዝገብ የሚችለውም ሁሉም የማህበሩ አባላት የተገመተውን የግንባታ ወጪ 50% በውጭ ምንዛሪ /በዶላር፣ በዩሮና በፓውንድ/ በምዝገባ ወቅት መክፈል ሲችሉ እና መሬት ተዘጋጅቶ ማህበሩ ሲረከብ የቀረውን 50% ሙሉ በሙሉ በመክፈል የግንባታ ፈቃድ ለመውሰድ ዝግጁ ሲሆኑ ብቻ ይሆናል፡፡
- ማህበሩ የእያንዳንዱን አባል የተሟላ ሰነድና ገንዘብ ወደ ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ገቢ ያደረጉበትን ደረሰኝ በማያያዝ በኤምባሲው ወይም ሚሲዮኑ በሚያመቻቸው የምዝገባ ቦታ ዘንድ በአካል ተገኝተው ምዝገባ ያካሂዳሉ፡፡
- ኤምባሲው የተደራጁ ማህበራትን ሙሉ መረጃ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ለዳያስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጄኔራል በፓውች ይልካል፡፡ ዳይሬክቶሬት ጄኔራሉም የማህራቱ ሰነድ ስለመድረሱ ለኤምባሲው ያሳውቃል፡፡
- በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የዳያስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጄኔራል የማህበራቱን ሙሉ መረጃ ከሸኚ ደብዳቤ ጋር ለመረጡት ክልል/ከተማ አስተዳደር እንዲያደርሱ ለማህበራቱ ተወካዮች ስለመቀበላቸው አስፈርሞ ያስረክባል፡፡
- ክልሉ/ከተማ አስተዳደሩ ለማህበራቱ እውቅና መሰጠቱን፣ መሬትና የግንባታ ፈቃድ መዘጋጀቱን በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ለዳያስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጄኔራልና ለማህበራቱ ተወካዮች ያሳውቃል፡፡
- በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የዳያስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ለመኖሪያ ሕብረት ሥራ ማህበሩ እውቅና መሰጠቱን እንዲሁም መገኘቱን፣ ለማህበሩ መሬትና የግንባታ ፈቃድ መዘጋጀቱን ለኤምባሲው ይገልጻል፡፡
- ኤምባሲው ይህንኑ ለማህበራቱ ያሳውቃል፡፡
- ማህበሩ ሁሉም አባላት ቀሪውን 50% ወደ ማህበራቱ ዝግ አካውንት ማስተላለፋቸውን በማረጋገጥ መረጃውን ለኤምባሲው ያሳውቃል፡፡
- ኤምባሲው ቀሪውን 50 በመቶ ክፍያ ፈጽመው ያጠናቀቁ ማህበራት መረጃ ለዳያስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ያስተላልፋል፡፡
- የዳያስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ቀሪውን 50% ክፍያ ፈጽመው ያጠናቀቁ ማህበራት መረጃ ለማህበሩ ተወካዮችና ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ያሳውቃል፡፡
- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የማህበሩ አባላት ለቤቱ ግንባታ የሚያስፈልገውን 100% በውጪ ምንዛሪ ማስገባታቸውን፣ ቀጥሎም በብር ወደ ማህበሩ በማህበሩ አካውንት መተላለፉን በማረጋገጥ ለክልሉ/ከተማ አስተዳደሩ የማህበራት አደራጅ አካልና ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ዳያስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች ዳ/ጄኔራል ያረጋግጣል፡፡
- የክልሉ/ከተማ አስተዳደሩ አደራጅ አካል ማህበራቱ የግንባታውን 100% ከፍለው ማጠናቀቃቸውን ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ማረጋገጫ ሲደርሰው ለማህበራቱ መሬትና የግንባታ ፈቃድ እንዲሰጣቸው ለሚመለከተው አካል ደብዳቤ ይልካል፣ ለማህበራቱ ተወካዮች በግልባጭ ያሳውቃል፡፡
- በክልሉ/ከተማ አስተዳደሩ መሬትና የግንባታ ፈቃድ የሚሰጥ ቢሮ ለማህበራቱ መሬትና የግንባታ ፈቃድ በአገር ቤት ለማህበራት ተወካይ አመራር አባላት ያስረክባል፣

- አገር ቤት የማህበራት ተወካይ አመራሮች ከሚመለከተው አካል መሬትና የግንባታ ፈቃድ በመረከብ ከወኪላቸው ጋር በመነጋገር ወደ ግንባታ ይገባል፣

## 3. <u>የባንክ ሂሳብ አከፋፈት</u>

- በቤት ልማት ኘሮግራሙ ለመሳተፍ የሚፈልጉ የዳያስፖራ አባላት በግላቸው በአገር ቤት በንግድ ባንክ የውጭ ምንዛሪ አካውንት እንዲከፈትላቸው የተዘጋጀውን ቅጽ በመሙላት ለኤምባሲው ጥያቄ ያቀርባሉ፡፡
- ኤምባሲው የደረሱትን የዳያስፖራ አባላት የውጭ ምንዛሪ የባንክ ሂሳብ እንዲከፈትላቸው ያቀረቡትን ጥያቄ ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ያስተላልፋል፡፡
- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ከኤምባሲው በደረሰው መረጃ መሠረት ለዳያስፖራ አባላቱ የግል የባንክ ሂሳብ በመክፈት ለኤምባሲው ያሳውቃል፡፡
- ኤምባሲው ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የደረሰውን የአካውንት መረጃ በኤምባሲው ዘንድ ለተመዘገቡ የዳያስፖራ አባላት ያሳውቃል፡፡
- የዳያስፖራ አባላቱ በኤምባሲው በኩል የደረሳቸውን የግል የባንክ አካውንት በመጠቀም ለመረጡት የመኖሪያ ቤት የግንባታ ወጪ የቅድሚያውን 50 በመቶ በውጭ ምንዛሪ ያስተላልፋሉ፡፡

## 4. <u>ገንዘብ ከግል የዳያስፖራ የውጭ ምንዛሪ ወደ ማህበሩ ዝግ የብር አካውንት የሚገባበት ሁኔታን በተመለከተ</u>

- ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር/ኤምባሲው/ በተሰጠው ውክልና መሠረት ኤምባሲው ለማህበራቱ ዝግ የብር የማህበር አካውንት እንዲከፈት ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የማህበራቱን መረጃ በማያያዝ ይጠይቃል፣
- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ኤምባሲው ባቀረበው ጥያቄ መሠረት ለማህበራቱ ዝግ የብር ሂሳብ በመክፈት ለኤምባሲው ያሳውቃል፣
- ኤምባሲው ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በደረሰው መረጃ መሠረት ለማህበራቱ የተከፈቱ የአካውንቶች ቁጥሮች ለየማህበራቱ አመራር አባላት በመግለጽ ሁሉም የማህበሩ አባላት የቤቱ የግንባታ ወጪ 50% እንዲያስገቡ ያሳውቃል፡፡
- የማህበሩ አመራር አባላት ከዚህ ቀደም በግላቸው በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ከከፈቱ የውጭ ምንዛሪ አካውንት ወደየተደራጁበት ማህበር ዝግ የብር አካውንት እንዲያስገቡ ያሳውቃሉ፣
- የዳያስፖራ አባላቱም ከዚህ ቀደም በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ከከፈቱት የግል የውጭ ምንዛሪ አካውንት ወደተከፈተው የማህበራቸው ዝግ የብር አካውንት የግንባታውን ወጪ 50% ገንዘብ እንዲገባ ያዛሉ፣
- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በደረሰው ትእዛዝ መሠረት ከዳያስፖራ አባላቱ የግል አካውንት ወደ ማህበራቱ ዝግ የብር አካውንት ያስገባል፣
- የማህበራት አመራር አባላት ሁሉም የማህበሩ አባላት የቤቱ የግንባታ ወጪ 50% ወደ ማህበሩ አካውንት አስገብተው ሲያጠናቅቁ ማጠናቀቃቸውን ለሚሲዮኑ ያሳውቃሉ፣
- ኤምባሲው የቤቱን የግንባታ ወጪ 50% ከግል አካውንታቸው ወደ ማህበራቱ አካውንት አዛውረው ያጠናቀቁ ማህበራት መረጃ ማህበራቱ የእውቅና ማረጋገጫ ሰርተፍኬት እንዲሰጣቸው ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክና ለዳያስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ይልካል፣
- የዳያስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጄኔራል 50% ክፍያ ክፍለው ያጠናቀቁ የማህበራትን መረጃ ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክና ለክልሉ/ከተማ አስተዳደሩ ማህበራት አደራጅ አካል ይሰጣል፣

- መረጃው ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና ዳያስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጀኔራል የደረሰው የክልል/ከተማ አስተዳደር የማህበራት አደራጅ አካል ለማህበራት የእውቅና ማረጋገጫ ሰርተፍኬት በማዘጋጀት ለዳያስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጀኔራል ይልካል፣
- የዳያስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጀኔራል የእውቅና ማረጋገጫ ሰርተፍኬቱን ለኤምባሲው ይልካል፣
- ኤምባሲው የደረሰውን የእውቅና ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ለማህበሩ አመራር አባላት ያሳውቃል፣
- የማህበራት አመራር አባላት ሁሉም የማህበሩ አባላት የቤቱ ቀሪውን 50% ወደ ማህበሩ አካውንት አስገብተው እንዲያጠናቅቁ ያደርጋሉ፣ ሁሉም አባላት ክፍያውን ሲያጠናቅቁ ማጠናቀቃቸውን ለሚሲዮኑ ያሳውቃል፣
- ኤምባሲው ቀሪውን 50% ክፍያ ፈጽመው ያጠናቀቁ ማህበራትን መረጃ ለዳያስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጀኔራል ያስተላልፋል፣
- የዳያስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጀኔራል ቀሪውን 50% ክፍያ ፈጽመው ያጠናቀቁ ማህበራትን መረጃ ለክልሉ/ከተማ አስተዳደሩ አደራጅ አካል፣ ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና ለአገር ቤት ማህበራት ተወካይ አመራሮች ያሳውቃል፣
- የክልሉ/ከተማ አስተዳደሩ አደራጅ አካል ማህበራቱ የግንባታውን 100% ከፍለው ማጠናቀቃቸውን ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ማረጋገጫ ሲደርሰው ለማህበራቱ መሬትና የግንባታ ፈቃድ እንዲሰጣቸው ለሚመለከተው አካል ያሳውቃል፣
- በክልሉ/ከተማ አስተዳደሩ መሬትና የግንባታ ፈቃድ የሚሰጥ ቢሮ ለማህበራቱ መሬትና የግንባታ ፈቃድ በአገር ቤት ለማህበራት ተወካይ አመራር አባላት ያስረክባል፣
- አገር ቤት የማህበራት ተወካይ አመራሮች ከሚመለከተው አካል መሬትና የግንባታ ፈቃድ በመረከብ ከወኪላቸው ጋር በመነጋገር ወደ ግንባታ ይገባል፣

## 5. <u>የቤቶች ዲዛይንና ግንባታ</u>

### 5.1 የቤቶች ዲዛይን

ሁሉም ክልሎችና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የዳያስፖራ መኖሪያ ቤት ዲዛይን በማዘጋጀት ለማህበራት ያቀርባሉ፡፡ የምዝገባ ሂደቱን አጠናቀው መሬት እና የግንባታ ፈቃድ የተሰጣቸው ማህበራት ዲዛይንና ግንባታን በተመለከተ ሁለት አማራጮች ይኖራቸዋል፡፡ እነርሱም፡-

- ክልሉ/ከተማ አስተዳደሩ ባዘጋጀው ዲዛይን መሠረት ዲዛይኑን መቀበላቸውን በማረጋገጥ ወደ ግንባታ መግባት፣
- የተደራጁት የዳያስፖራ ማህበራት የክልሉ/ከተማ አስተዳደሩ ባለው የአካባቢ ፕላን መሠረት የራሳቸውን ዲዛይን አዘጋጅተው ማቅረብ ይችላሉ፡፡ የማህበራቱ አባላት ያቀረቡትን የዲዛይን ማሻሻያ በክልሉ/በከተማ አስተዳደሩ አግባብነት ባለው አካል ሲፀድቅ ወደ ግንባታ መግባት ይችላሉ፡፡ በዲዛይን ለውጥ የሚፈጠር የዋጋ ልዩነት ካለ የየማህበራቱ አባላት ከግንባታ በፊት በማህበራቱ ዝግ አካውንት ያስገባሉ፡፡

### 5.2 የቤቶች ግንባታ

የዲዛይን ሂደቱን ያጠናቀቁ ማህበራት ክልሉ/ከተማ አስተዳደሩ ባዘጋጀው ዲዛይን ወይም ራሳቸው አዘጋጅተው ባስጸደቁት ዲዛይን መሠረት ወደ ግንባታ ለመግባት ሁለት አማራጮች ይኖራቸዋል፡- እነሱም

- በክልሉ/ከተማ አስተዳደሩ ባዘጋጀው ዲዛይን ወይም ማህበራቱ በራሳቸው አዘጋጅተው አቅርበው ባስፀደቁት ዲዛይን መሠረት ግንባታው በመንግሥት አካል እንዲካሄድ ማድረግ ይችላሉ፡፡ ግንባታው በመንግሥት እንዲገነባላቸው የወሰኑ ማህበራት

ግንባታውን ከሚያካሂደው የክልሉ/ከተማ አስተዳደሩ አካል ጋር የግንባታ ውል ይፈጽማሉ፡፡ ማህበራቱ በግላቸው አዘጋጅተው ባቀረቡት ዲዛይን መሠረት ግንባታው በመንግሥት አካል የሚካሄድ ከሆነ በዲዛይን ለውጥ ምክንያት የግንባታው ወጪ የሚጨምር ከሆነ ልዩነቱን ለማህበሩ በተከፈተው ዝግ ሂሳብ ሙሉ በሙሉ በማስገባት ግንባታውን ከሚያካሂደው የክልሉ/ከተማ አስተዳደሩ አካል ጋር የግንባታ ውል ስምምነት ይፈራረማሉ፡፡ ግንባታውን ለማካሄድ ውል የገባው አካል በውል መሠረት ግንባታውን ያካሂዳል፡፡

- ክልሉ/ከተማ አስተዳደሩ ባዘጋጀው ዲዛይን ወይም ማህበራቱ በራሳቸው አዘጋጅተው ባስፀደቁት ዲዛይን መሠረት ግንባታውን በፈለጉት ተቋራጭ /ኮንትራክተር/ ማስገንባት ይችላሉ፡፡ ግንባታው የሚካሄደው ማህበራቱ አዘጋጅተው በፀደቀላቸው ዲዛይን መሠረት ከሆነ በዲዛይን ለውጥ የቤቱ ዋጋ ላይ ጭማሪ ካለው ሁሉም የማህበሩ አባላት ተጨማሪውን ገንዘብ በማህበሩ ዝግ ሂሳብ በማስገባት ወደ ተግባር መግባት ይችላሉ፡፡

## 6. በማህበራት ስም ለቤቶች ግንባታ በዝግ ሂሳብ የተቀመጠን ገንዘብ ስለማንቀሳቀስ

- የመኖሪያ ቤት ሕብረት ስራ ማህበራት የባንክ ሂሳብ በመተዳደሪያ ደንቡና በክልሉ/ከተማ አስተዳደሩ ማህበራት እንዲያደራጅ ሥልጣን የተሰጠው አካል፣ በማህበሩ አመራር አካላት ወይም በተወካዮች አማካኝነት እንዲንቀሳቀስ ሲፈቀድና ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ደብዳቤ ሲጻፍ የሚንቀሳቀስ ይሆናል፡፡

## 7. የቤቶች የዲዛይንና ግንባታ ቁጥጥርና ክትትል

የቤቶች ዲዛይንና ግንባታ በመንግሥትም ሆነ ማህበራት በሚመርጡት የግል ተቋራጭ /ኮንትራክተር/ የሚካሄድ ቢሆንም ክልሎችና ሁለቱ ከተማ አስተዳደሮች የቤቶች የዲዛይንና የግንባታ ቁጥጥርና ክትትል የሚያደርጉበትን የተጠናከረ አሰራር ይዘረጋሉ፡፡ በዚህም መሠረት፦

- የክልሉ/ከተማ አስተዳደሩ የቤቶች ዲዛይንና ግንባታ ቁጥጥርና ክትትል እንዲያደርግ ሥልጣን የተሰጠው አካል ለቤቱ የሚቀርቡ ዲዛይኖችን ያፀድቃል፡፡
- የቤቶች የግንባታ ሂደትና የሚገነቡ ቤቶች በፀደቀው ዲዛይን መሠረት መሆኑን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣
- የቤቶች ግንባታ የደረሰበትን ደረጃ አስመልክቶ ወቅቱን የጠበቀ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለሚመለከተው አካል ይልካል፡፡
- የተገነቡ የመኖሪያ ቤቶች በዲዛይኑ መሠረት የጥራት ደረጃቸውን ጠብቀው መገንባታቸውን በማረጋገጥ ግንባታቸው የተጠናቀቁ ቤቶች በመመሪያውና በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት እንዲፈጸም ያደርጋል፡፡

## 8. የመኖሪያ ቤቶች ርክክብ

- በማህበር የተደራጁ አባላት የመኖሪያ ቤት ርክክብን በተመለከተ ማህበሩ ግንባታውን ከሚያከናውነው አካል ጋር በገቡት ስምምነት መሠረት የሚፈጸም ሲሆን፣ ለእያንዳንዱ አባል የቤት ርክክብ የሚፈጸመው ግን በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ይሆናል፡፡
- በግል ተመዝግበው በሦስተኛ አካል በመኖሪያ ቤት ሕብረት ስራ ማህበራት እንዲደራጁ የተደረጉ አባላት በተመዘገቡበት የቤት አይነት መሠረት በየቤቱ ዓይነት በእጣ ይከፋፈላሉ፡፡

9. **<u>እንደየክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ ተጨማሪ መስፈርቶች</u>**

- **<u>አማራ ክልል</u>**፡- በአባልነት ለተመዘገቡበት ማህበር እንዲሰጥ ከተወሰነው የከተማ ቦታ ላይ ለሚለቁት ተነሽ ባለይዞታዎች የሚከፈለውን ካሳ እንዲሁም ነባር ግንባታዎችና ንብረቶችን ከስፍራው ለማንሳትም ሆነ ለመሠረተ ልማት አውታሮች ዝርጋታ የሚያስፈልጉትን ሌሎች ወጪዎች በቅድሚያ መክፈል የሚችል፣
- **<u>ኦሮሚያ ክልል</u>፡-** በመሃል ከተማ በመልሶ ማልማት ኘሮግራም በተያዘ ቦታ ላይ የመኖሪያ ቤት ማህበር ሆኖ የሚደራጅ ማህበር ወይም ዩኒየን ከሆነ የከተማ መሬት ልማትና ማኔጅመንት በሚያወጣው ግምት መሠረት ቤታቸው ለሚፈርስባቸው ሰዎች ካሳ ለመክፈል ቃል የሚገባ፣

1. <u>የክልሎች/ከተማ መስተዳድሮች የመኖሪያ ቤቶች ዓይነት፣ የአንድ ቤት ስፋት፣ የግንባታ ወጪ እና የማህበር አባላት ብዛት ማሳያ ሠንጠረዥ</u>

| የመኖሪያ ቤቶች ዓይነት | የመኝታ ቤት ብዛት | በክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የአንድ ቤት መነሻ ዋጋ (በኢት/ብር) እና የቦታ ስፋት (በካሬ ሜትር) | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ትግራይ | | አማራ | | ኦሮሚያ | | ሶማሌ | | ደ/ብ/ብ/ሕ | | ጋምቤላ | | ሐረሪ | | ቤኒሻንጉል ጉሙዝ | |
| | | የቦታ ስፋት | የግንባታ ዋጋ ግምት | የቦታ ስፋት | የግንባታ ዋጋ ግምት | የቦታ ስፋት | የግንባታ ዋጋ ግምት | የቦታ ስፋት | የግንባታ ዋጋ ግምት | የቦታ ስፋት | የግንባታ ዋጋ ግምት | የቦታ ስፋት | የግንባታ ዋጋ ግምት | የቦታ ስፋት | የግንባታ ዋጋ ግምት | የቦታ ስፋት | የግንባታ ዋጋ ግምት |
| በኢፓርትመንት (G+3፣ G+4 እና ከዚያ በላይ) | ባለሁለት መኝታ | 74 | 424390.00 | 74 | 424500.00 | 80 | 400000.00 | 74 | 532800.00 | 80 | 770720.98 G+4 | 74 | 424390.00 | 74 | 424390.00 | 74 | 424390.00 |
| | | | | | | | | | | 85 | 840208.61 G+3 | | | | | | |
| | ባለሦስት መኝታ | 100 | 573500.00 | 100 | 573500.00 | 100 | 550000.00 | 100 | 720000.00 | 95 | 824911.15 G+4 | 114 | 693120.00 | 100 | 573500.00 | 100 | 573500.00 |
| | | | | | | | | | | 100 | 926571.12 G+3 | | | | | | |
| | ባለአራት መኝታ | 136 | 779960.00 | 136 | 779960.00 | 110 | 700000.00 | 136 | 927200.00 | 110 | 876049.35 G+4 | 150 | 912000.00 | 136 | 779960.00 | 136 | 779960.00 |
| | | | | | | | | | | 115 | 959128.58 G+3 | | | | | | |
| | ከፍተኛ ህንፃ | | | 56 ሰዎች ከተደራጁ በመሃል ከተማ ከፍተኛ ህንጻ ግንባታ ይፈቀዳል | | በዩኒየን ለሚደራጁ በመሃል ከተማ ከፍተኛ ህንጻ ግንባታ ይፈቀዳል | | 48 ሰዎች ከተደራጁ በመሃል ከተማ ከፍተኛ ህንጻ ግንባታ ይፈቀዳል | | | | | | በዩኒየን ለሚደራጁ በመሃል ከተማ ከፍተኛ ህንጻ ግንባታ ይፈቀዳል | | 48 ሰዎች ከተደራጁ በመሃል ከተማ ከፍተኛ ህንጻ ግንባታ ይፈቀዳል | |

| የመኖሪያ ቤቶች ዓይነት | የመኝታ ቤት ብዛት | በክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የአንድ ቤት መነሻ ዋጋ (በኢት/ብር) እና የቦታ ስፋት (በካሬ ሜትር) | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ድሬዳዋ | | አማራ | | ኦሮሚያ | | ሶማሌ | | ደ/ብ/ብ/ሕ | | ጋምቤላ | | ሐረሪ | | ቤኒሻንጉል ጉሙዝ | |
| | | የቦታ ስፋት | የግንባታ ዋጋ ግምት | የቦታ ስፋት | የግንባታ ዋጋ ግምት | የቦታ ስፋት | የግንባታ ዋጋ ግምት | የቦታ ስፋት | የግንባታ ዋጋ ግምት | የቦታ ስፋት | የግንባታ ዋጋ ግምት | የቦታ ስፋት | የግንባታ ዋጋ ግምት | የቦታ ስፋት | የግንባታ ዋጋ ግምት | የቦታ ስፋት | የግንባታ ዋጋ ግምት |
| በታውን ሃውስ (G+0 ወይም G+1 ወይም G+2) | ባለሁለት መኝታ | 128 | 582400.00 | | | | | 74 | 424390.00 | 90 | 840076.79 G+2 | 114 | 693120.00 | | | | |
| | | | | | | | | | | 80 | 204544.70 G+0 | | | | | | |
| | ባለሦስት መኝታ | 160 | 728000.00 | 114 | 693120.00 | | | 100 | 573500.00 | 105 | 912422.86 G+2 | 150 | 912000.00 | 114 | 693120.00 | 114 | 693120.00 |
| | | | | | | | | | | 90 | 242378.78 G+0 | | | | | | |
| | ባለአራት መኝታ | 200 | 910000.00 | 150 | 912000.00 | 80 | 800000.00 | 136 | 779960.00 | 120 | 956890.70 G+2 | | | 150 | 912000.00 | 150 | 912000.00 |
| | | | | | | | | | | 100 | 278736.00 G+0 | | | | | | |
| | ባህላዊ ኪነ ህንፃ (ባለ 4 መኝታ) | | | | | | | | | | | | | 129.63 | 788150.00 G+2 | | |
| | ባህላዊ ኪነ ህንፃ (ባለ 6 መኝታ) | | | | | | | | | | | | | 181.18 | 1101574.00 G+1 | | |
| | ባህላዊ ኪነ ህንፃ (ባለ 7 መኝታ) | | | | | | | | | | | | | 247.55 | 1505104.00 G+2 | | |

<u>መፍቻ</u>፡ ዩኒየን ሁለት እና ከዚያ በላይ የህብረት ስራ ማህበራት በአንድ ላይ ሲደራጁ የሚፈጥሩት አደረጃጀት ነው፡፡

**2. <u>የአንድ የቤት ማህበር አባላትን ብዛት በተለያዩ አማራጭ የመኖሪያ ቤት አይነትና መኝታ ቤት ብዛት የሚያሳይ ሰንጠረዥ</u>**

**2.1 በአፓርትመንት (G+3፣ G+4 እና ከዚያ በላይ) ሲሆን፣**

| የክልሎችና ከተማ መስተዳድሮች ዝርዝር | በተለያዩ አማራጮች የአንድ ቤት ቦታ ስፋት በካሬ ሜትር | | | የአንድ ማህበር አባላት ብዛት | የአንድ አፓርትመንት ቦታ ስፋት በካ.ሜ | አስተያየት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ባለሁለት መኝታ | ባለሦስት መኝታ | ባለአራት መኝታ | | | |
| **አማራጭ አንድ** | | | | | | |
| ትግራይ | | | | 12 እስከ 24 | | |
| አማራ | 4/80 ካ.ሜ | 6/88 ካ.ሜ | 4/96 ካ.ሜ | 14 | 1232 ካ.ሜ | |
| ኦሮሚያ | | | | 12 እስከ 24 | | |
| ሶማሌ | 3/80 ካ.ሜ | 6/88 ካ.ሜ | 3/96 ካ.ሜ | 12 | 1056 ካ.ሜ | |
| ደ/ብ/ብ/ሕ G+4 | 3/80 ካ.ሜ | 6/95 ካ.ሜ | 3/110 ካ.ሜ | 12 | 1140 ካ.ሜ | |
| ደ/ብ/ብ/ሕ G+3 | 3/85 ካ.ሜ | 4/100 ካ.ሜ | 3/115 ካ.ሜ | 10 | 1000 ካ.ሜ | |
| ጋምቤላ | 3/80 ካ.ሜ | 6/88 ካ.ሜ | 3/96 ካ.ሜ | 12 | 1056 ካ.ሜ | |
| ሐረሪ | 3/80 ካ.ሜ | 6/88 ካ.ሜ | 3/96 ካ.ሜ | 12 | 1056 ካ.ሜ | |
| ድሬዳዋ | | | | | | |
| ቤኒሻንጉል ጉሙዝ | 3/80 ካ.ሜ | 6/88 ካ.ሜ | 3/96 ካ.ሜ | 12 | 1056 ካ.ሜ | |
| **አማራጭ ሁለት** | | | | | | |
| ትግራይ | | | | | | |
| አማራ | | 7/88 ካ.ሜ | 7/96 ካ.ሜ | 14 | 1288 ካ.ሜ | |
| ኦሮሚያ | | | | | | |
| ሶማሌ | | 6/88 ካ.ሜ | 6/96 ካ.ሜ | 12 | 1104 ካ.ሜ | |
| ደ/ብ/ብ/ሕ G+4 | | 6/95 ካ.ሜ | 6/110 ካ.ሜ | 12 | 1230 ካ.ሜ | |
| ደ/ብ/ብ/ሕ G+3 | | 5/100 ካ.ሜ | 5/115 ካ.ሜ | 10 | 1075 ካ.ሜ | |
| ጋምቤላ | | 6/88 ካ.ሜ | 6/96 ካ.ሜ | 12 | 1104 ካ.ሜ | |
| ሐረሪ | | 6/88 ካ.ሜ | 6/96 ካ.ሜ | 12 | 1104 ካ.ሜ | |
| ድሬዳዋ | | | | | | |
| ቤኒሻንጉል ጉሙዝ | | 6/88 ካ.ሜ | 6/96 ካ.ሜ | 12 | 1104 ካ.ሜ | |

| የክልሎችና ከተማ መስተዳድሮች ዝርዝር | በተለያዩ አማራጮች የአንድ ቤት ቦታ ስፋት በካሬ ሜትር | | | የአንድ ማህበር አባላት ብዛት | የአንድ አፓርትመንት ቦታ ስፋት በኪ.ሜ | አስተያየት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ባለሁለት መኝታ | ባለሦስት መኝታ | ባለአራት መኝታ | | | |
| **አማራጭ ሦስት** | | | | | | |
| ትግራይ | | | | | | |
| አማራ | | 8/88 ኪ.ሜ | 6/96 ኪ.ሜ | 14 | 1280 ኪ.ሜ | |
| ኦሮሚያ | | | | | | |
| ሶማሌ | | 8/88 ኪ.ሜ | 4/96 ኪ.ሜ | 12 | 1088 ኪ.ሜ | |
| ደ/ብ/ብ/ሕ G+4 | | 8/95 ኪ.ሜ | 4/110 ኪ.ሜ | 12 | 1200 ኪ.ሜ | |
| ደ/ብ/ብ/ሕ G+3 | | 6/100 ኪ.ሜ | 4/115 ኪ.ሜ | 10 | 1060 ኪ.ሜ | |
| ጋምቤላ | | 8/88 ኪ.ሜ | 4/96 ኪ.ሜ | 12 | 1088 ኪ.ሜ | |
| ሐረሪ | | 8/88 ኪ.ሜ | 4/96 ኪ.ሜ | 12 | 1088 ኪ.ሜ | |
| ድሬዳዋ | | | | | | |
| ቤኒሻንጉል ጉሙዝ | | 8/88 ኪ.ሜ | 4/96 ኪ.ሜ | 12 | 1088 ኪ.ሜ | |

**2.2 በታውን ሀውስ (G+0 ወይም G+1 ወይም G+2) ሲሆን፣**

| የክልሎችና ከተማ መስተዳድሮች ዝርዝር | በተለያዩ አማራጮች የአንድ ቤት ቦታ ስፋት በካሬ ሜትር | | | የአንድ ማህበር አባላት ብዛት | የአንድ አፓርትመንት ቦታ ስፋት በኪ.ሜ | አስተያየት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ባለሁለት መኝታ | ባለሦስት መኝታ | ባለአራት መኝታ | | | |
| **አማራጭ አንድ** | | | | | | |
| ትግራይ | | | | | | |
| አማራ | 14/120 ኪ.ሜ | | | 14 | 1680 ኪ.ሜ | |
| ኦሮሚያ | (G+1 እና/ወይም G+2)/120 ኪ.ሜ | | | 12 እስከ 24 | | |
| ሶማሌ | 12/120 ኪ.ሜ | | | 12 | 1056 ኪ.ሜ | |
| ደ/ብ/ብ/ሕ | 3/60 ኪ.ሜ | 4/75 ኪ.ሜ | 3/90 ኪ.ሜ | 10 | 750 ኪ.ሜ | |
| ጋምቤላ | 12/120 ኪ.ሜ | | | 12 | 1440 ኪ.ሜ | |
| ሐረሪ | 12/120 | | | 12 | 1440 ኪ.ሜ | |
| ድሬዳዋ | 14/160 ኪ.ሜ | | | 14 | 1920 ኪ.ሜ | |

| የክልሎችና ከተማ መስተዳድሮች ዝርዝር | በተለያዩ አማራጮች የአንድ ቤት ቦታ ስፋት በካሬ ሜትር | | | የአንድ ማህበር አባላት ብዛት | የአንድ አፓርትመንት ቦታ ስፋት በካ.ሜ | አስተያየት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ባለሁለት መኝታ | ባለሦስት መኝታ | ባለአራት መኝታ | | | |
| ቤኒሻንጉል ጉሙዝ | 12/120 ካ.ሜ | | | 12 | 1056 ካ.ሜ | |
| **አማራጭ ሁለት** | | | | | | |
| ትግራይ | | | | | | |
| አማራ | | 14/135 ካ.ሜ | | 14 | 1890 ካ.ሜ | |
| ኦሮሚያ | | | | | | |
| ሶማሌ | | 12/135 ካ.ሜ | | 12 | 1620 ካ.ሜ | |
| ደ/ብ/ብ/ሕ | | | | | | |
| ጋምቤላ | | 12/135 ካ.ሜ | | 12 | 1620 ካ.ሜ | |
| ሐረሪ | | 12/135 ካ.ሜ | | 12 | 1620 ካ.ሜ | |
| ድሬዳዋ | | 14/200 ካ.ሜ | | 14 | 2400 ካ.ሜ | |
| ቤኒሻንጉል ጉሙዝ | | 12/135 ካ.ሜ | | 12 | 1620 ካ.ሜ | |
| **አማራጭ ሦስት** | | | | | | |
| ትግራይ | | | | | | |
| አማራ | | | 14/150 ካ.ሜ | 14 | 2100 ካ.ሜ | |
| ኦሮሚያ | | | | | | |
| ሶማሌ | | | 12/150 ካ.ሜ | 12 | 1800 ካ.ሜ | |
| ደ/ብ/ብ/ሕ | | | | | | |
| ጋምቤላ | | | 12/150 ካ.ሜ | 12 | 1800 ካ.ሜ | |
| ሐረሪ | | | 12/150 ካ.ሜ | 12 | 1800 ካ.ሜ | |
| ድሬዳዋ | | | 14/250 ካ.ሜ | 14 | 3000ካ.ሜ | |
| ቤኒሻንጉል ጉሙዝ | | | 12/150 ካ.ሜ | 12 | 1800 ካ.ሜ | |